# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ግብአቶች፦ BLB, JEA, JEA-RB, JEA-RC, JEE, KLA-RA

ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦ Chief Financial Officer/ዋና የፋይናንስ ኃላፊ
Chief Operating Officer ዋና የሥራ ኃላፊ
Deputy Superintendent of School Support and Improvement የት/ቤት ድጋፍ እና መሻሻል ምክትል ዋና ተቆጣጣሪ

## ክፍያን መሰረት ያደረገ የትምህርት ምዝገባ

I. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በክፍያ ተማሪዎችን መመዝገብ እና እንደአስፈላጊነቱ ክፍያ የሚሠረዝላቸውን የመለየት ሂደት መስፈርት እና ሥርአት ማበጀት።

ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመግባት ስለሚመዘገቡ ተማሪዎች ትክክለኛ የመኖሪያ ቦታ እና ብቁነት መመዘኛ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ/Montgomery County Board of Education Policy JEA ተደንግጓል ነዋሪነት/Residency፣ የትምህርት ክፍያ/Tuition፣ እና ምዝገባ/Enrollment እና MCPS Regulation JEA-RB፣ የተማሪዎች ምዝገባ/Enrollment of Students።

II. ትርጉም

A. ትክክለኛ የመኖሪያ ቦታ–የአንድ ሰው ትክክለኛ ወይም እውነተኛ መኖሪያ፣ ተአማኒነት ያለው፣ ጊዜያዊ መኖሪያን ወይም በ MCPS ነፃ ትምህርት ለመከታተል የተመቻቸ የሚል ዓላማን ያላካተተ ማለት ነው። ይሁን እንጂ፣ አሁን ባለው የመኖሪያ ቦታ ላልተወሰነ ጊዜ ወይም በቋሚነት የመኖር ዓላማ የግድ አስፈላጊ አይደለም። የአንድን ሰው ትክክለኛ የመኖሪያ ቦታ ለመወሰን በእርግጠኝነት ላይ የተመሠረተ እና በየግለሰቡ(ቧ) ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

B. ችግሮች – የትምህርት ክፍያን ለማስቀረት የሚያስችሉ ያልተለመዱ እና በወላጅ/ሞግዚት ሙሉ በሙሉ የተመዘገቡ ልዩ ሁኔታዎች። ለምቾት ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በነፃ ለመማር ዓላማ የተወጠኑ ሁኔታዎችን አያካትትም።

C. ብቁ ተማሪ - የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ወይም ዜግነት የሌላቸው፣ 18 ዓመት ዕድሜ የሞላው(ት) ወይም ከ18 ዓመት እድሜ አስቀድሞ ራስን የመምራት ፈቃድ የተሰጠው/የተሰጣት፣ ነገር ግን በትምህርት ዓመት የመጀመሪያ ቀን እድሜው(ዋ) ከ20 ዓመት የማይበለጥ ተማሪ።

III. በትምህርት ክፍያ የምዝገባ ሂደት

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን ደንብ "MCPS Regulation JEA-RB" የማያሟሉ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች/ብቁ ተማሪዎች፣ የተማሪዎች ምዝገባ/Enrollment of Students፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ክፍያ ተማሪን ለማስመዝገብ ወይም ራሳቸው ለመመዝገብ የሚፈልጉ ይህንን ቅጽ "MCPS Form 335-73A" መሙላት አለባቸው፣ ነዋሪነት የሌለው/የሌላት ተማሪ በትምህርት ክፍያ የምዝገባ ጥያቄ/Request to Enroll Nonresident, Tuition-paying Student፣ ዓለምአቀፍ ምዝገባ እና ምደባ "International Admissions and Enrollment (IAE)"።

1. በካውንቲው ነዋሪ ላልሆኑ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ወይም ብቁ ተማሪዎች የተለየ ትምህርት ቤት ለመጠየቅ ይችላሉ፣ ነገር ግን የምደባ ሁኔታን በተመለከተ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መብቱ የተጠበቀ ነው። ለሚመርጡት ት/ቤት የትምህርት ክፍያ ለመክፈል የቤተሰብ ፈቃደኛ መሆን የቦታ ምደባ ዋስትና አይሰጥም።

2. IAE የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ "MCPS Form 335-73A" በማየት ከ Office of School Support and Improvement (OSSI) እና ከተጠየቀው ት/ቤት ርእሰመምህር/ት ጋር በመነጋገር የሚከተሉትን ምክንያቶች መሠረት ያደረገ ውሳኔ ይሰጣል።

a) በክፍል ውስጥ የተማሪ መጠን መመሪያ

b) በክፍል ደረጃ ምዝገባ

c) አቅምን መሠረት ያደረገ-ምዝገባ

d) የምዝገባ እሳቤዎች-ግምቶች

e) የትምህርት ቤት እና የክለስተር አቅም

f) የህንፃ አጠቃቀም

g) ትምህርታዊ ፕሮግራሞች

h) የሠራተኛ ምደባ

i) የርእሰመምህርት አስተዋጽኦ

B. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎችን በማሳደጊያ ወይም በቡድን የሚያኖሩ ከስቴት ውጪ የሆኑ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲዎች MCPS Form 335-73 ማቅረብ አለባቸው፣ Determination of Residency and Tuition Status፣ እና MCPS Form 335-73A፣ Request to Enroll Nonresident Tuition-paying Student፣ ለ IAE።

1. ከስቴት ውጪ በሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ አማካይነት የሚመደቡ ተማሪዎች IAE ከ OSSI እና ከፑፒል ሠራተኞች እና የተማሪዎች የትምህርት ክትትል ጽ/ቤት፣ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጋር በመነጋገር የተወሰነ ካልሆነ በስተቀር በሞንትጎመሪ ካውንቲ አሳዳጊ ወይም የጋራ መኖሪያ ቤት አካባቢ በሚገኝ ትምህርት ቤት ይመደባሉ።

2. ተማሪው(ዋ) በሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ማሳደጊያ በማደጎ እንዲያድግ/እንድታድግ የተሰጠ(ች)በት ማስረጃ ለ IAE ካልቀረበ በስተቀር፣ ከስቴት ውጪ የሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ ለሚያስገባው ከነዋሪነት ክልል ውጪ ለሆነ(ች) ተማሪ ይከፍላል። እንደዚህ አይነት ዶኩመንት ከቀረበ፣ የትምህርት ክፍያ ስረዛ ይደረጋል።

C. ስለ ትምህርት ክፍያ በየዓመቱ በቦርድ ይወሰናል።

D. ሙሉ የትምህርት ክፍያ መጠን ለተማሪ በአማካይ የሚወጣውን የወጪ ግምት የብድር እዳ አገልግሎትን ጨምሮ እኩል ይሆናል፣ እና ተማሪዎችን በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ለማስተማር የሚወጣውን ትክክለኛ የወጪ መጠን ያንፀባርቃል።

E. ልዩ ትምህርት ወይም ሌላ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለሚያገኙ ተማሪዎች፣ መደበኛው የዓመት ክፍያ ለተጨማሪ አገልግሎት የብድር አገልግሎትን ጭምር ለመስጠት በተገመተው ያህል ወጪ መጠን ይጨምራል።

F. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ውጪ ለሚኖሩ የ MCPS ሠራተኞች ልጆች የሙሉ ጊዜ የትምህርት ዓመት ክፍያ መጠን እና/ወይም የሰመር ስኩል ክፍያ አንድ አይነት የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ እና ተመሣሣይ አገልግሎት ከሚያገኙ ከሌሎች በካውንቲው ነዋሪነት ከሌላቸው ተማሪዎች የክፍያ መጠን ግማሽ ይሆናል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ክፍያ ለመፈጸም ከፔይሮል ተቀናሽ እየተደረገ እንዲከፈል ወይም የትምህርት ዓመቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ የዓመቱ ክፍያ በጠቅላላ መክፈል አለባቸው።

G. የትምህርት ክፍያዎች

1. ከዚህ በታች በሰክሽን III.H.1. or III.H.3 ከተገለጹት ውስጥ አንዱን ሁኔታ ካላሟሉ በስተቀር፣ ተማሪው(ዋ) ለተመዘገበ(ች)በት የገባ(ች)በት ወይም የለቀቀ(ች)በትን ጊዜ ሳይጨምር ለሙሉ ሴሚስተር ሙሉ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።

2. የትምህርት ክፍያ መጠንን በተመለከተ መረጃዎች ከ "IAE" ወይም ከ "Division of Controller in the Office of the Chief Financial Officer" ማግኘት ይቻላል።

3. የ MCPS ሠራተኞች ካልሆኑ የትምህርት ክፍያ በሴሚስተር ወይም በየዓመቱ ይፈጸማል። የመጀመሪያው ሴሚስተር የትምህርት ክፍያ ከኦገስት 1 ይፈጸማል እና ለሁለተኛው ሴሚስተር የትምህርት ክፍያ ከዲሴምበር 31 በፊት ይፈጸማል።

4. የትምህርት ክፍያዎች በወቅቱ ካልተከፈሉ፣ ባልተከፈለው ሂሳብ ላይ በወር አንድ ፐርሰንት ወለድ ተጨምሮ ይከፈላል። የትምህርት ክፍያ ካልተከፈለ ተማሪው(ዋ) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንዲወጣ/እንድትወጣ ይደረጋል እና ያልተከፈለው ገንዘብ እንዲሰበሰብ ወደ ኮሌክሽን ኤጀንሲ ይተላለፋል።

5. በትምህርት ዓመቱ የገባ(ች) ተማሪ እና ዘግይቶ ክፍያ አለመፈጸሙ ከታወቀ፣ ተማሪው(ዋ) የትምህርት ክፍል ከመቀጠሉ(ሏ) በፊት መፈጸም ይኖርበታል።

6. F-1 visa የያዙ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ መሠረት "MCPS Regulation JEA-RC" አስቀድሞ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፣ ዓለምአቀፍ የውጪ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ/Enrollment and Placement of International and Foreign Students

H. ተመላሽ ክፍያ እና በተመዛዛኝ ክፍያ

1. በተመዛዛኝ የትምህርት ክፍያ ወይም በተመዛዛኝ ተመላሽ ክፍያዎች ሊፈጸሙ የሚችሉት በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው፡-

   a) ተማሪው(ዋ) ነዋሪ መሆኑ(ኗ)ን ታሳቢ በማድረግ ወይም IV.C ክፍያ እንዲሠረዝለት/እንዲሠረዝላት ባለሙብት የሆነ(ች) ለማናኛውም ያክል ጊዜ በቅድሚያ የተደረገ የትምህርት ክፍያ፣ ወይም

   b) ተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት በሚመዘገብበት/በምትመዘገብበት ወቅት ነዋሪ ከነበረ(ች) እና በኋላ ላይ ነዋሪነት ከለቀቀ(ች) እና ከካውንቲው ውጪ እየኖረ(ች) በክፍያ ለመመዝገብ ከጠየቀ(ች)፣ ወይም

   c) ተማሪው(ዋ) ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ድኩልስ (MCPS) የተባ(ች)ው ከስቴት ውጪ በሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ አማካይነት ከሆነ እና ትምህርት ከተጀመረ የመጀመሪያው ቀን በኋላ ገብቶ/ታ ከሆነ፣ እና/ወይም ሴሚስተሩ ከመጠናቀቁ የመጨረሻ ቀን በፊት የለቀቀ(ች) ከሆነ።

2. በ III.H.1 በተገጸው የክፍያ ምዝዝን መሠረት የዓመቱን የትምህርት ክፍያ መጠን በትምህርት ቀኖች ብዛት እየተካፈለ የአንድ ቀን ሂሳብ መጠን ይሠላል፣ ከዚያም ተማሪው(ዋ) በተማረ(ች)ባቸው ቀኖች እየተባዛ የክፍያ ምዝዝን/prorated ይደረጋል ።

   a) ተመላሽ ክፍያዎች መሠረት የሚደረጉት በይፋ የመውጣት-የለቀቁበትን/withdrawal ቀንን ነው።

   b) በ MCPS እስካሉ ድረስ ተማሪዎች ሳይሳተፉ ለቀሩባቸው የትምህርት ቀኖች ተመላሽ ክፍያ አይፈጸምም።

3. ርእሰመምህር/ተወካይ የመግቢያውን ሁኔታ ተስማምቶ(ታ)በት ወስኖ(ና) ከሆነ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ክፍያ/Tuition ለሙሉ ኮርስ ከሚከፈለው ያነሰ ምዝዝን/prorated ሊደረግ ይችላል። የተመዛዘነ የጊዜ ሠሌዳ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

   a) አንድ ኮርስ --25 ፐርሰንት ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

   b) ሁለተ ኮርሶች -- 50 ፐርሰንት ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

   c) ሦስት ኮርሶች -- 75 ፐርሰንት ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

   d) አራት ኮርሶች ወይም የበለጠ -- 100 ፐርሰንት ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

4. ከዚህ በላይ "III.H.1. ወይም III.H.3." ከተገለጹት ሁኔታዎች አንዳቸው ካልተሟሉ፣ የትምህርት ክፍያ ተመላሽ አይደረግም ወይም ተማሪው(ዋ) እየተማረ(ች) ባለበ(ች)በት ሴሚስተር የለቀቀ(ች)በት ቀን ጭምር ተቀናናሽ ምዝዝን/prorated አይደረግም።

I. የትምህርት ክፍያ መሰብሰብ

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቅጾች ከቀረቡ በኋላ፡- MCPS Form 335-73፣Determination of Residency and

Tuition Status፣ እና MCPS Form 335-73A፣ Request to Enroll Nonresident Tuition-paying Student፣የትምህርት ክፍያ ያልተከፈለ መሆኑን እና ምደባው የፀደቀ ከሆነ፣ Controller ሠራተኛ—

1. የቦርድን የክፍያ ውሳኔ መሠረት ያደረገ ተገቢ የትምህርት ክፍያ መጠን መወሰን፣

2. የ MCPS Form 335-73A ክፍል ሦስት/Part III በካውንቲው ነዋሪ ያለሆነ(ች) በክፍያ የሚማር/የምትማር ተማሪ Request to Enroll Nonresident, Tuition-paying Student

3. የክፍያ ሠነድ ለወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ መስጠት

4. የትምህርት ክፍያን መሰብሰብ፣

5. በየወቅቱ የትምህርት ክፍያ ገንዘብ ነክ አካውንቶችን ከ IAE ሪኮርዶች ጋር ማመሣከር፣

6. የትምህርት ክፍያ (በሙሉ ወይም በተፈቀደ የክፍያ ፕላን መሠረት) መፈጸም ካለበት 30 ቀኖች ውስጥ ያልተከፈለ ከሆነ—

    a) ባልተከፈለው መጠን-ሂሣብ ላይ ወለድ ማስላት ይጀመራል፣

    b) ክፍያ ላልፈጸሙ ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ወለድ የተጨመረበት መሆኑን፣ ያልተከፈለ ገንዘብ ለሚሰበስብ ኤጀንሲ፣ እና/ወይም ከክፍል የመባረር ሁኔታ ሊከተል እንደሚችል ማሳወቅ፣ እና

    c) ለትምህርት ቤት እና በ IAE መኖሪያ ቤት ስፔሻሊስት ማሳወቅ።

## IV. የትምህርት ክፍያ መስፈርቶችን ስለመሠረዝ

A. በ MCPS Regulation JEA-RB ላይ ባለው ድንጋጌ መሠረት፣ የተማሪዎች ምዝገባ/Enrollment of Studentsእድሜው(ዋ) ከ18 ዓመት በታች የሆነ እና በፍርድ ቤት ውሳኔ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ከሆነ(ች) ሞግዚት፣ ወይም ሌላ አዋቂ ሰው፣ ይፋዊ ለሆነ ዝምድና ግንኙነት ሁኔታዎች ብቁ የማያደርጉ፣ እና ወላጆች/ሞግዚቶች በሞንትጎመሪ ካውንቲ መደበኛ ነዋሪ ያልሆኑ፣ ለማስመዝገብ የሚፈልጉ፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች ክፍያ ለመሠረዝ አግባብነት ካለው ለመወሰን ለ" IAE" ማማከር ያስፈልጋል።

B. IAE እያንዳንዱን በካውንቲ ነዋሪ ያልሆነ(ች) ተማሪ በአንዳንድ ከባድ ሁኔታ/ቀውስ መፈጠሩን የሚያረጋግጥ ደጋፊ የጽሑፍ ማስረጃ ሲቀርብ የክፍያ መስፈርት እንዲሠረዝ ይወስናል። በ IAE የሚሰጡት ድንጋጌዎች በየዓመቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ እንደገና ይገመገማል።

C. የትምህርት ክፍያን ለመሠረዝ የሚያስችል ቀውስ ማለት በምክንያት በቤተሰብ ላይ የሚደርስ ከባድ ችግር

1. የወላጅ/ሞግዚት መሞት፣ በህልፈተ ሕይወት ሠርተፊኬት ወይም በሌላ ማስረጃ የተረጋገጠ፣

2. ወላጅ/ሞግዚት በጽኑ ህመም ላይ መሆን፣ በኃኪም ማስረጃ የተረጋገጠ፣ ማስታወሻ፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ፣

3. ወላጅ/ሞግዚት የእፅ ሱሰኝነት፣ በህክምና ባለሙያ የተረጋገጠ የጽሑፍ ማስረጃ፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ፣

4. ወላጅ/ሞግዚት በእስር ቤት መኖራቸውን ከሚመለከተው ህጋዊ አካል፣ ከእስር ቤት፣ ወይም ሌላ የጽሑፍ ማረጋገጫ፣

5. ወላጅ/ሞግዚት ለውትድርና አገልግሎት የተመደበ(ች) ከሆነ፣ የጽሑፍ ወታደራዊ ትእዛዝ፣ ወይም ሌላ ማረጋገጫ፣ ወይም

6. ያልተለመዱ እና በእርግጠኝነት የተማሪ የመማር ፍላጎቶችን ወይም ጤንነትን የሚቀንሱ/ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች፣ በጽሑፉ በግልጽ የሚረጋገጥ እና ተማሪን ካልተለመደ እና ከሚያባብሱ ሁኔታዎች ጋር በማገናኘት የመኖሪያ ቦታ ማዘጋጀት አስፈላጊ የሚሆንበትን ሁኔታ።

D. ተማሪ አብሯቸው ያለ(ች) ነዋሪ የትምህርት ክፍያ መስፈርቶች እንዲሠረዙለ(ላ)ት ለመጠየቅ የሚከተለውን ማቅረብ አለበ(ባ)ት

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህጋዊ/መደበኛ ነዋሪነት ማረጋገጫ፣

2. ያጋጠመውን ከባድ ችግር/ቀውስ ሁኔታ የሚገልጽ እና የተማሪው(ዋ)ን ኃላፊነት ለሌላ ነዋሪ ማስተላለፋቸውን የሚያረጋግጥ በወላጅ/ሞግዚት የተፈረመበት እና ኖቶራዝ የተደረገ ደብዳቤ፣

3. የተፈጠረውን ከባድ ችግር/ቀውስ ማረጋገጫ የጽሑፍ ማስረጃ፣

4. ስለ ተማሪው(ዋ) ኃላፊነት ከሚቀበል/ከምትቀበል ነዋሪ የተፈረመበት እና ኖቶራይዝ የተደረገበት ደብዳቤ፣ እና/ወይም

5. በፍርድ ቤት የተመደበ(ች) የሞግዚትነት ዶኩመንቶች፣ አግባብነት ካለው

E. ከባድ ሁኔታ/ቀውስ በመፈጠሩ ምክንያት የትምህርት ክፍያ መስፈርቶች እንዲሠረዙ የተጠየቀበት የተሟላ ዶኩመንት በቀረበ 10 የሥራ ቀኖች ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። ሁኔታዎቹ በተለይ ውስብስብ ከሆኑ፣ ለወላጆች/ሞግዚቶች በማሳወቅ ጊዜው ሊራዘም ይችላል።

V. ***ይግባኝ የመጠየቂያ ሥርአት/ሂደት***

በቦርድ ፖሊሲ Board Policy JEA መሠረት፣ ነዋሪነት፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ/Residency, Tuition, and Enrollment፣ ስለ ነዋሪነት ወይም የትምህርት ክፍያ ስረዛ መስፈርቶችን በሚመለከት የተሰጠ ውሳኔ ይግባኝ ሲጠየቅ በ MCPS Regulation KLA-RA መሠረት መሞላት አለበት፣ ከህዝብ ስለሚቀርቡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት/Responding to Inquiries and Complaints from the Public።

A. IAE፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ የይግባኝ ሂደቱን ለማፋጠን በተለይም ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ከሆነ እና ተማሪ ክፍል ለመከታተል እየተጠባበቀ(ች) ከሆነ በውሳኔ ሂደቱ ላይ ድጋፍ ይሰጣል።

B. ወላጅ-ወላጆች/ሞግዚት-ሞግዚቶች የይግባኝ ሂደቱ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ተማሪው(ዋ) ክፍል ገብቶ/ታ እንዲማር-እንድትማር የሚፈልጉ ከሆነ ከዓመቱ የትምህርት ክፍያ 10 በመቶ መክፈል ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው ውሳኔ ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ የትምህርት ክፍያው/Tuition በሙሉ ወይም በከፊል ተመላሽ ይደረጋል።

**ስለዚህኛው ደንብ *ታሪክ*፡-** ቀደም ሲል "Regulation No 560-1" ይባል የነበረው ፌብሩዋሪ 26/1981 ተሻሽሎ ወደ ሁለት ደንቦች ተከፋፍሏል (ይህኛው እና JEA-RC) ኦገስት 26/1987ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር12/1992 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 6/2001 ተሻሽሏል፣ ማርች 8/2005 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 15/2013 ቀደምሲል MCPS Regulation JED-RA ይባል የነበረው ተሻሽሎ በድጋሚ MCPS Regulation JEA-RE ተብሏል፣ በትምህርት ክፍያ የሚደረግ ምዝገባ/Tuition-based Enrollment፣ ኤፕሪል 3/2019።